ታክሳስ ፳፫ ቀን ፳፻ ዓ.ም (Jan 2, 2008)

# እዞም ሰለስቲ ተጋዳላይ ተጋዳሊት እንታይ ጉዱ!

## ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ምስኪን!

(ከአያልነሽ)

እነኝህ "አረናዎች" በጣም የሚገርሙ በጣም የሚደንቁ፣
ምን ቢሰለጡኑ፣ ምን እጅግ ቢመጥቁ፣
ሱፍ ከረባት አስረው፤ በሪሽን ቢደምቁ፣
እዚያው ከቆሙበት ኢንች እንኳን አራቁ።
ስዬ፣ አረጋሽና፣ ገብሩ አስራት 3 ሆነው፣
አቤት ጉድ በሚያሰኝ ቃናቸው አንድ ነው፤
ምን ዓይነት እርግማን ምን ዓይነት ጣጣ ነው?
3ቱም ተጋዳላይ 3 አስርታት ደፍነው፣
ዛሬም የሚያሳቡት በድንጋይ ዘመን ነው።

ምስኪን!

የወያኔ ሰዎች በተለይም መሪ የነበሩ አብዛኛዎቹ፤ ማሰብ የሚባለውን ነገር ካቆሙ ብዙ ጊዜያቸው ነው። ይህንን አባባሌን የሚያጠናክሩልኝ ብዙ ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ። የወያኔን ሰዎች አብዛኛዎቹን ስለማንኛውም ነገር ስትጠይቋቸው ወይ ስታወሯቸው የሚመልሱትና የሚያወሩት ዛሬ በ2000 ዓ.ም ላይ በምንገኝበት እዚያው ትናንትና ሕወኃት/ወያኔ ሲመሰረት በነበረበት ጊዜ ላይ ሆነው ነው። ዛሬም እዚያው ላይ እንደቆሙ ናቸው። ይሄ ታዲያ አያሳዝንም? ይሄ ደግሞ ያለምክንያት አይደለም። ይህንን የምለውን እውነት የሚያረጋግጡልኝ ብዙ ማስረጃዎች ቢኖሩኝም በወያኔ/ህወሓት ድርጅት ውስጥ እስከ 1981 ዓ.ም(ኢ.ትዮ.አ) ድረስ አባል ሆነው የቆዩት አቶ ካህሳይ በርሄ በእንግሊዝኛ ካሳተሙት " Ethiopia, Democratization and Unity (The Role of the Tigray people's Liberation Front) - ኢትዮጵያ፥ ዴሞክራሲያዊ ሂደትና አንድነት (የህወሓት ሚና) በሚል መጽሐፋቸው ውስጥ በሰፊው ያቀረቡ ሲሆን ለአብነት ያህል አንድ ሁለቱን እጠቅሳለሁ

> "ህወሓት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሆኖ አያውቅም። አባላቱ (ተራ አባላቱ) መሪዎቻቸውን በነጻ ለመምረጥ መብት አልነበራቸውም።" (ገጽ 60) "ጎዕሽ እውነተኛ ስሙ ዮሐንስ ተ/ኃይማኖት የ ቲ.ኤል.ኤፍ (የትግራይ ሓርነት ግንባር) የማዕከላዊ ኮሚቴ አመራር አባል የነበረ ሲሆን በ1968(እንደ ኢ.ትዮ.አ) ከሌሎቹ የማዕከላዊ ኮሚቴ አመራር ጋር በሕወሓት ተገድሏል። ሕወሓት ከ ት.ሓ.ግ.(ቲ.ኤል.ኤፍ) ጋር ለመዋሃድ የውሸት/አስመሳይ ስምምነት አደረገ። የ ት.ሓ.ግ.(ቲ.ኤል.ኤፍ) አባላት ውሕደቱን ተቀብለው ብረታቸውን/ትጥቃቸውን አስረክበው ያለምንም መጠራጠር ተኙ፤ የሕወኃት ልዩ ታጣቂዎች ግን ተዘጋጅተው በመቆየት(በተኙበት) አሰሯቸው፣ ገደሏቸው" ይላል። ገጽ 62 ላይም።

"አረናዎች"በቅርቡ ደግሞ በፈረንጆች ዘመን መለወጫ ማገባደጃ ላይ በ ዲሴምበር 28 እና 29 ዓርብና ቅዳሜ ከቪ.ኦ.ኤ ራዲዮ ባልደረባ አዳነች

ፍሥሐዬ ጋርም ''ምይይጥ'' አድርገዋል። ስለ ቆይታቸው ወደ በኋላ ላይ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። ገብሩ አሥራት፣ አረጋሽ፣ ስዬ ...ወዘተ፣ ከህወሓት/ወያኔ እነርሱ ''ወጥተናል'' ለገሰ ዜናዊ ደግሞ ''አባረርኩ'' የሚላቸው እነኝህ ግለሰቦች ''አረና'' በሚል ''ነጻ'' አውጪ ሆነን መጥተናል ሲሉ ገና ከጅምሩ ''የማይሆን ነገር ለሚሰትህ አትንገር'' በሚል መልዕክቴን ለማስተላለፍ ሞክሪያለሁ። መልዕክቴ/ትችቴ ለእነርሱ የማይጥምና የማይመች ሊሆን ቢችልም እኔ ግን ስለ እውነት የምነገራቸው፣ እነ ገብሩ አስራት ህወሓት/ወያኔ የሚባለው ድርጅት ውስጥ ከገቡ ጀምሮ በሥነ ልቡና ጭንቀት ውስጥ የሚገኙና የሚሰቃዩ ሰዎች መሆናቸውን ስለምረዳ ነው። ይሄ የሥነ-ልቡና ጭንቀታቸው ደግሞ በመለስ ከድርጅታቸው ህወሓት/ወያኔ ከተባረሩ በኋላ ይበልጥ መባባሱ ግልጽ ነው። ከተባረሩ በኋላ ደግሞ በመለስ መዳፍ ሥር ናቸው። ያልዘሩት አያጭዱም ተብሏልና። በመሆኑም እንቅስቃሴያቸው በሙሉ እስካሁን የሄዱበትና የሚሄዱበት መንገድ ጤነኛ ያልሆነና በደመ ነፍስ የሚናውዙ እንደሆነም ስለምረዳ ነው። ከዚህ የደመ ነፍስ እንቅስቃሴ እንዴት ይውጡ ከሚል ጭንቀት ነው ሁሌም ሃሳቤን ላካፍላቸውና ልጠቁማቸው የምሞክረው።  እነኝህ ግለሰቦች ''አረና አሉ ፆሮና'' በምንም ስም ይምጡ በምን ''ነፃ አውጪ'' ነን የሚሉት ነገር ግን ማንንም ''ነፃ'' እንደማያወጡና ይልቁንም ራሳቸው ከሥነ-ልቦና ጭንቀታቸው ''ነፃ'' ሊወጡ ይገባቸዋል እላለሁም። እንድ እኔ እምነት ''አረናዎች'' መጀመሪያውንም ''ነጻ'' አይደሉም በሥነ-ልቡና። ሥነ-ልቡናቸው የታወከው ደግሞ በቀድሞ ''ነፃ አውጪ'' ድርጅታቸው በወያኔ ውስጥ ከልጅነት እድሜያቸው ጀምሮ ረዥሙን የዕድሜ ዘመናቸውን በዚሁ ድርጅት ባሳልፉበት ወቅት፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ መላ አካላቸውን በደም ውስጥ በመንከራቸው ነው። ይህ ዕውነታ ነገር ሲነሳና (በቅርቡም በቪኦኤ ላይ ሲጠየቁ ሰምቻለሁና) እየሸሹት ግን እየተከተላቸውና ሊያልፉት የማያስችላቸው ሁኔታ ስለሚያጋጥማቸው፣ በተለመደው ደባብቆና አድበስብሶ የማለፍ ዘይቤአቸው ''ያለፈ ነገር ማንሳቱ ጠቀሜታው ባይታየንም'' በማለት ስለሚጠየቁ ብቻ ሊመልሱ ይገደዳሉ። ሁለት ወዶ አይሆንም ''አረናዎች'' ። አዲሱን ድርጅታችሁን ''በአረና'' ስም ማስተዋወቅ ተፈልጎ ከጥያቄ መሸሽ ደግሞ አይቻልም። ''መጀመሪያ ባልዘፍንሽ፣ ከዘፍንሽ ባላፈርሽ'' ይባል የለ!  እርግጥ ''ወይን''፣ ራዲዮ ፋና፣ ''ድምፂ ትግራይ'' ወዘተን.... ለለመዳችሁ ''አረናዎች''፣ በሌሎች ነጻ ራዲዮኖች ሆነ ነጻ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች ስትቀርቡ መንገዱ ላይመች ይችላል። ግን...ብዙ ያደረጋችሁ ናችሁና  ለዚህ የሚሆን ድፍረት ታጣላችሁ አልልም። ከጀመራችሁ ደግሞ ወደፊትም በሌሎችም ነጻ ፕሬሶች መጠየቅ አይቀርምና፣ ድፍረታችሁን አበረታታለሁ። ''አረናዎች'' ሆናችሁ ወያኔዎች በአጠቃላይ መጀመሪያውኑም የሥነ ልቡና ተጠቂዎችና ሰለባዎች ናችሁ፤ ይሄን በቅድሚያ ማመን አለባችሁ። ሌላው በዚሁ ችግር ''የአረናዎች'' የሥነ ልቡና ጥቃት ይበልጥ ከወዳያኞቹ ወያኔዎች ከፍ የሚያደረገው፣ ''አረናዎች'' ከሚወዱት ድርጅታቸው ሕውሓት/ወያኔ ሳይፈልጉ ግን በእነ መለስ ተቀድመው ተዋርደው በመባረራቸው፣ የሥነ-ልቦና ጥቃቱን ይበልጥ ከፍ ያደርገዋል።  ልዩነቱ ይሄ ነው። በግልባጩ እንየውና እነ ስዬ፣ እነ መለስን ቀድመው ቢሆን ኖሮ የሚሆነው አሁን በእነርሱ ላይ የደረሰው በእነ መለስ ላይ

ይሆንና፣ እነ ሰዬ ደግሞ የነመለስን ቦታ ይዘው ያው አሁን በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚደርስበትን አምባገነናዊ በትርና የተሸከመውን ግፍ በዚሁ መንግድ ከማስቀጠል የሚቀየር ነገር አይኖርም። ለዚህ የሥነ-ልቡና ደዌ ምክንያቱ ደግሞ ወያኔ የሚባለው ድርጅት እንደ ድርጅት ሲመሰረት ጀምሮ በደም የተጨማለቀ በመሆኑ ነው። እንደ ሥነ-ልቡና ተመራማሪዎችና ጠበብቶች አባባል፣ አንዴ ሰውን በመግደል ህይወቱን የጀመረ ሰው ከዚያ በኋላ መግደልን እንደ ተራ ነገር አድርጎ ይወስድና ሰዎችን መግደል፣ ማጥፋት፣ ማሳደድ እንድስራ ይቆጥረዋል ይላሉ። ጠበብቶቹ እንድ እነኝህ አይነት ሰዎች ድርጊቱን እንደ ጥሩና ጤነኛ ነገር አድርገው ስለሚመለከቱት፣ ሰዎችን ማሰቃየትና የሰዎችን ሲቃ ማዳመጥ እጅግ ያረካቸዋል፣ በሲቃቸውም ይደሰታሉ ይላሉ። በመግደላቸው፣ ሰዎችን በማጥፋታቸው ይረካሉ፣ በማለትም ይገልጿቸዋል። ለዚህ የጠበብቶች አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የራሳችን መንግስቱ ኃ/ማርያም ነው። መንግስቱ ያን ሁሉ ወጣት አርደና ጨፍጭፎ ''እኔ እንኳን ሰው ዝንብም አልገደልኩ'' ማለቱን እናስታውሳለን። የድሮዎቹ ወያኔዎች የአሁኖቹ ''አረናዎች'' በየራዲዮኖች እንደሚያቀርቡትና ዛሬ ደግሞ በቅርቡ ዲሴምበር 28/29 2007 ዓ.ም(ፈርንጆች አ) ቪኦኤ ላይ እንዳስረዱት ይሆን ማንነታቸው? ''አረናዎች'' በሄዱበት የታሪክ ጉዟቸው ላይ ከተመዘገበ ታሪካቸው ውስጥ ሌላውን ማስረጃ እስቲ ላቅርብ፦

''<u>ከታሪካዊ አሻራዎች፥</u>

ሀ/<u>«ሰባቱ ጠላቶቻችን»-</u> የወያኔ ቡድን በትጥቅ ትግሉ ወቅት ታጋዩንና ህዝቡን ለመቀስቀስ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች መካከል ዘፈን ዋነኛው እንደነበር ይታወቃል። ዋና ዋናው ድርጊቶቹንና ፍፃሜዎቹን የሚዘክረው በዘፈን ነው። የወያኔ የታሪክ አሻራዎቹ ከዘፈኖቹ ሊገኙ ይችላሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም።

በ1972 ወይም በ1973 ላይ የወጣ «ሰባቱ ጠላቶቻችን» የሚል ዘፈን አለው። ይህ ዘፈን በበርሃው ዘመን በየቦታውና በየአጋጣሚው የሚደለቅ ተወዳጅ የቡድኑ ማስታወሻ ነበር። አሁን አሁን ዘመኑም ለዚያ ዘፈን የሚያመች ስላልሆነ የተቀለፈበት ይመስለኛል። የዚህ ዘፈን ይዘት ባጭሩ ሰባቱ ጠላቶቻችንን በየተራ እየደመሰስን ጀግንነታችንን አስመስክረናል፣ የሚደፍረን የለም የሚል መልዕክት ያለው ነው። ቁም ነገሩ ዘፈኑ ሳይሆን የተዘፈነበት ምክንያቱ ነው።

የወያኔ ቡድን የደመሰሰናቸው ሰባቱ ጠላቶቻችን ብሎ እንደሎጋው ሽቦ የገዳይ ዘፈን ያወጣላቸው ኃይሎች ኢዲዩ(ወይም የዛሬው ኢዴህፓ)፣ ኢህአፓ፣ ጀበሐ(በወያኔ አጠራር አማ)፣ የትግራይ አርነት ግንባር ወይም ቲ.ኤል.ኤፍ. የተባለ ከወያኔ እኩል ትግራይ ውስጥ ተመስርቶ ይንቀሳቀስ የነበረ ድርጅት፣ «ጠርናፊት» የተባለ እዚያው ትግራይ ውስጥ ተደራጅቶ ይንቀሳቀስ የነበረ የብሔር ድርጅት፣ የውስጥ አናርኪስቶች ወይም «ሓንፈሽቲ» ብሎ የሚጠራቸው በአንድ ወቅት በቡድኑ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ትግል አንስተው የነበሩ ተራማጅ ኃይሎች፣ እንዲሁም ደርግ-ኢሠፓ ናቸው። ከደርግ እኩል ጠላቶቻቸው የሆኑትን ስድስቱን ኃይሎች በሚመለከት፣ አምስቱን እንዳይነሱና ትግራይ ውስጥም እንዳይመለሱ አድርገው ያጠፏቸው መሆኑን፣ ጀብሐ ቀኑን እየጠበቀ መሆኑ እንደሆነና እንደማይቀርለት፣ ሰባተኛው ደርግ ደግሞ እየተደቆሰ መሆኑን የሚናገር ዘፈን ነው።

ዘፈኑ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ላይ በሙዚቃዊ ድራማ መልክ ሲቀርብ ደግሞ ነገሩን ሁሉ በይበልጥ የሚናገር ምስክር ይሆናል። በድራማው ዉስጥ ወያኔን የሚወክለውን የአንበሳ ገፀ ባሕርይ ይሰጡታል ። ሌሎችን ደግሞ የማስታውሰውን ያህል ለማስታወስ፣ ኢህአፓን-ነብር፣ ኢዲዩን-

ጅብ፣ ቲ.ኤል.ኤፍን ቀበሮ፣ ጅብሐን-ተኩላ....ወዘተ ያደርጓቸዋል። የሚሰጧቸው የአውሬዎች ገፀ ባሕርያት ስለ ድርጅቶቹ ወያኔ የነበረውን አስተሳሰብም የሚያመላክት ነው። ከዚያም አንበሳው ወያኔ በዘፈኑ እየታጀበ፣ ገሚሱን በክርን <u>እየደቆሰ ሲያደባየው</u> ገሚሱን እያሳደደ ከኋላ እየቦጫጨቀ <u>ከትግራይ ምድር ሲያስወጣው</u> ያሳይና ደርግ ደግሞ ቀሳስሎ ሲያነክስ ያሳያል። (በጊዜው ደርግ ገና አልወደቀም ነበርና !) አንበሳው ወያኔና ተኩላው ጅብሐ ደግሞ ሲያልፉ-ሲያገድሙ እየተናከሱ ይቆዩና አንበሳው ቀይ ጠብቀኝ ሲለው ይታያል። (ጀብሓን የወጉት በ1974 ነበርና !)

«ሰባቱ ጠላቶቻችን» የሚለው ከላይ በጥቂቱ ለማሳየት የሞከርኩት ሙዚቃዊ ድራማ በከፍተኛ መቀስቀሻነት የወያኔ ቡድን ሲጠቀምበት የነበረ፣ የጠረኝነትና የፀረ- ሕብረት ባሕርዩን የሚያጋልጥ ታሪካዊ ገድሉ ነው። (ታሪኩ በደም ለወየበ ድርጅት የ ''ብሔራዊ ኤርቅ'' ጥሪ ? ? ? ጎህ ቅጽ 2 ቁ14/93 ዓ.ም. ከመሃሪ ዮሐንስ።) ይላል የጥቅሱ መጨረሻ።

ተጋዳላይ ገብሩ አስራትና ተጋደልቲ አርጋሽ አዳነ ከአዳነች ፍስሃዬ ጋር ቆይታ ባደረጉበት ወቅት ላነሳችላቸው በርካታ ጥያቄዎች አንድም ሳይመልሱ ግን ደግሞ ''አረና'' ትግራይን ለማስተዋወቅ ደፋ ቀና ይላሉ።
እስቲ በምይይጣቸው ወቅት ከተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎች አንዳንዶቹን በአጭሩ ላንሳ።

ጥያቄ፥ ''አረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት'' በፖለቲካ ፓርቲ ደረጃ ተመዝግቦ ተመስርቱዋል፤ ግን ጽሁፎቹን ስናይ በፊት ከነበረው ከህወሓት የሚለይበትን ለመረዳት ትንሽ ከበድ ያለ ይመስላልና ''አረና ትግራይ'' ከሕወሓት የሚለይበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የ''አረና ትግራይ'' መሪ የሆኑት ገብሩ አሥራት የተለመደውን መልስ ሰጥተዋል። በአጭሩ የሚሉት ምንም ልዩነት የለውም ልዩ የሚያደርገው ትልቅ ነገር በተግባርና ሊያስፍጽማቸው በሚፈልገው ጉዳዮች ላይ ለዚያ ያለው ቁርጠኝነት ካልሆነ በስተቀር በማለት ገልጠውታል። ''አረናዎች'' ኢትዮጵያ ውስት አሁን በተግባር የሚሰራውን ሕገ-ወያኔ እንዳለ ይስማሙበታል። ለዚህም ነው ጋዜጠኛዋም የራሷን አስተያየት ሰጥታ ስትደመድም ''እንደተባለው በመንግሥታዊ አወቃቀሩ ላይ ምንም ልዩነት ያላችሁ አይመስለኝም አሁን ካለው መንግሥት ጋር'' በማለት ወደ ሌላ ጥያቄ የገባችው። እንዲያው ለጨዋታው ከላይ በተንደረደርኩበት መሰረት እነ መለስ ቀድመው ''አረናዎችን'' በሏቸው እንጅ የዛሬዎቹ ''አረናዎች'' የትናንቶቹ ወያኔዎች ናቸው። እነ ገብሩ አስራት፣ አረጋሽና እስዬ አብርሃ...ወዘተ ቀድሞ በነበሩበት ድርጅት፣ በውስጣቸው የተፈጠረን ችግርና እንቅስቃሴ እንዲሁም ችግሩን ፈጣሪ ናቸው ያሏቸውን ሰዎች እየገደሉ እዚህ የደረሱ፣ ዛሬ እነሱ ያ እጣ ሳይደርሳቸው በመባረር ብቻ መገላገላቸውና መተርፋቸው ተመስገን ሊሉ ይገባል። ከዚህ ውጪ ግን የሚያደረጉት እንቅስቃሴ ሆነ ''ነፃ'' አውጪነት በእነመለስ/ስብሃት ወያኔ እግር ሥር የወደቀና በእነርሱ ትእዛዝ የሚንቀሳቀስ ነፍስ የሌለው እቃ ነው። ምስኪኖቹ ''አረናዎች'' የተለየ ነገር ያቀረቡትና ከነመለስ የተሰጣቸው፣ አዲስ <u>ስም</u> ብቻ ነው ''አረና ትግራይ'' የሚለው! ቂ ቂ ቂ ቂ ቂ ቂ አፈር ልብላ!!! ጠላትሽ አፈር ይብላ እንዳትሉኝ ''አረናዎች'' አደራ። ጠላቴ የእናንተ ወዳጅ ነውና! ጉድ እኮ ነው ''አረና''፣ያሮና እንኳንስ ትግራይን

ራሳቸውንም ''ነፃ'' አያወጡበት። እንዲች እንዳሉ ይሞታሉ፤ መለስ እያዘዛቸው። ሌላውን አንገብጋቢ ጥያቄ ደግሞ እስቲ እንዴት እንደሚመልሱት እንመልከት!

**ጥያቄ፥** ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የሰፈረው የብሔር ብሄረ-ሰቦች ራሳቸውን ችለው ማስተዳደር እስከመገንጠል ድረስ የሚለው አለ፤ አሁንም ይሄ እስከመገንጠል ድረስ የሚለው ብዙ ሰው በጥሩ ዓይን አይመለከተውም ሊከፋፍል ይችላል፣ አደገኛ ነው ......ይቀጥላል